# ውለታ

ሥነ ቃልን ተጎናጽፈው
        በብዕር ወዝ በጻዳሉ
የፊደል ጮራ ፈንጥቀው
        ከብርሃኑ ያካፈሉ
ማስተዋልን ተመርኩዘው
        የዕውቀት ችግኝ የተከሉ
የልማድን ኬላ ሰብረው
        አዲስ ክሥተት ያበቀሉ
የዕድገት ራእይ እንዲያብብ
        መሥዋዕትነት የከፈሉ
መክሊታቸውን አብዝተው
        የጽሑፍን ሀብት ያቀበሉ
በምግባራቸው ጸንተው
        ትውልድ ለማነጽ የታገሉ
ቁዋሚ ቅርስ ወርሰው ያወረሱ
        ምንኛ ናቸው የታደሉ?
ለኢትዮጵያ ሻማ ሆነው
ከዕድልዋ ተቆካልፈው
ከዕጣዋ ተቆራኝተው
        ለእርስዋነትዋ ክብር ታጭተው
ለነፃነት ዋጋ ከፍለው
        አዲስ ተስፋ አመንጭተው
በጽኑነት ተገንብተው
        ቆራጥነትን አጥልቀው
ትሕትናን ተካብሰው
        ፈሪሀ እግዚአብሔርን ታጥቀው
ስጦታቸውን አክብረው
        ውርሳቸውን ጠብቀው
በዘመናት የማይመክን
        ድርሳነ ጥበብ አፍልቀው፤
የዕውቀትን ሐውልት የተከሉ
        ትውልድ አንጸው ያደረሱ
ምንኛ ናቸው የታደሉ
        ቁዋሚ ቅርስ ወርሰው ያወረሱ . . .
ምንኛ ናቸው የታደሉ።

___________

ለክቡር አቶ ሀዲስ አለማየሁ

ከ«ፈተና፤ የዕንባ ጉዞዎች እና ሌሎች ግጥሞች»፥ 1997 ዓ.ም. (2005)፥ ገጽ 79-80
ቴዎድሮስ አበበ
http://www.tewodros.com